# የማይለቀን የቅማንት ጉዳይ፤ ብለው ብለው ወደኛ ለአቤቱታ መጡ!

አንዱዓለም ተፈራ - የእስከመቼ አዘጋጅ
ሰኞ፤ ነሐሴ ፳፰ ቀን፤ ፳፲፫ ዓመተ ምህረት

አቶ ጥላሁን ጀምበር፤ ነሐሴ ፳ ፻ ፫ ዓመተ ምህረት፤ **<u>የአማራ ክልል መንግስት በቅማንት ጉዳይ የሰጠዉ ዉሳኔ ከሕገ-መንግስት መስፈርቶች አንፃር ሲገመገም፤</u>** በሚል ርዕስ ያወጡትን ጦማር በኢትዮሜዲያ አነበብኩ። አቶ ጥላሁን ጀምበር በሚያምኑበት ሕገ-መንግሥት ደንብ፤ ሕገ-መንግሥቱን ባረቀቀውና ባጸደቀው መንግሥት፤ ይሄንን ሕገ-መንግሥት በሥራ ላይ አውሎ በሚተገብረው አስተዳደር፤ ጉዳያቸውን ማቅረብና መከራከር ሙሉ መብታቸውን ነው። ይህንን ጽሑፍ ማቅረባቸውም ለሚያምኑበት ዓላማ ማራመጃቸው በማድረግ ነው። አቶ ጥላሁን ጀምበር ለምን ይሄን እምነት ያዙ? ወይንም ለምን ይሄን ጻፉ? ብዬ አልከራከርም። እሳቸው የተነሱትም ሆነ የሚፋረዱት፤ ሕገ-መንግሥቱን ተንተርሰውና መረጃ አድርገው ነው። የኔ የዚህ ጽሑፍ መነሻ ሁለት ማጠያየቂያዎች ናቸው። አንደኛ፤ ጥያቄውም ሆነ መልሱ አሁን ኢትዮጵያን በሚያስተዳድረው ባለሥልጣን መንግሥት ሥር እያለ፤ ለምን በውጩ የብዙኀን መገነኛዎች ይሄ ጦማር እንዲሰራጭ ተደረገ? የሚለው ነው። ሁለተኛው ደግሞ፤ ይሄን በሀገራችን ያለ ገዥ ባለሥልጣን፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሠረታዊ ብሎ የተቃወመባቸው የፖለቲካ ፍልስፍናና የአስተዳደር መመሪያው በጥያቄ ውስጥ እያሉ፤ የዚህ ጦማር መልዕክት ምንድን ነው? የሚለው ነው። እንግዲህ አንባቢ እንዲረዳልኝ፤ እኔ የምነሳው፤ ከሕገ-መንግሥቱ አኳያ፤ አቶ ጥላሁን ጀምበር ትክክል ናቸው ወይንም አይደሉም ከሚል የሕግ ጠበቃነት ሳይሆን፤ ከፖለቲካ መልዕክቱና ግንዛቤው አንጻር፤ ለምን? የሚለውን ተንተርሼ ነው። እሳቸው ሕግ፤ እኔ ደግሞ ፖለቲካ! ማን የበላይ እንደሆነ አንባቢ ይገንዘቡልኝ።

በመጀመሪያ ደረጃ፤ ይህ የቅማንቶችና ባካባቢው ያሉ አማራዎች የግል ጉዳይ አይደለም። የስልጢ ጉዳይ የስልጢና የሌሎች ጉራጌዎች የግል ጉዳይ አይደለም። የአማራው ሰውነት በጉምዞች መበላት፤ የአማራውና የጉሙዙ ብቻ ጥያቄ አይደለም። ማንኛውም በገዥው አምባገነን ወገንተኛ የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት የሚነሳ ጥያቄ፤ የያንዳንዳችን ኢትዮጵያዊያን ሀገራዊ ጥያቄ ነው። በተለያየ መንገድ፤ ተጠምዝዞም ሆነ ተጠምዛዞ ቢቀርብ፤ የሀገር የሕልውና ጥያቄ ነው። በርግጥ አምባገነኑ ወገንተኛ የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት፤ በመነጣጠል መግዛቱንና ለያንዳንዳችን የተለያየ የቤት ሥር መሥጠቱን አላባራበትም። እንደምናውቀው ሁላችን ባንድ ለበቅ እየተገፍን ነው። እናም ይህ ጉዳይ ሁላችንን ያገባናል። የሚያግደን ቢኖር፤ እንደ መለስ ዜናዊ፤ *“የአክሱም ሐውልት ለወላይታው ምኑ ነው?”* የሚለውን የምንቀበል ብንሆን ነው። ስለዚህ ይሄን ጉዳይ ለማንሳት፤ የግድ ቅማንት ወይንም ያካባቢው አማራ ሆኜ መገኘት የለብኝም። ስለዚህ ጉዳይ በጥልቅ አውቃለሁ፤ ከዚህ በፊትም አንድ ጽሑፍ አቅርቤበታለሁ።

ይህ የአቶ ጥላሁን ጦማር፤ ጠቅላላ በቅማንት ስም የተደረገውንና በመደረግ ላይ ያለውን የፖለቲካ ስሌት በግልጽ የያዘ በመሆኑ፤ በቀላሉ ሊታይና ሊታለፍ የሚገባው አይደለም። መሠረታዊ የሆነውን የአምባገነኑን የፖለቲካ ፍልስፍናና የአስተዳደር መመሪያ የያዘና አቀንቃኝ በመሆኑ፤ ትክክለኛ መልስ ሊሠጠው ይገባል። በዚህ ርዕስ ጉዳይ የቀረበው፤ የወገንተኛው አምባገነን የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር ቡድንና የኢትዮጵያ ሕዝብ የተፋጠጡበት፤ የሀገራችን ሕልውና ነው። ይህ ጽሑፍ በአቶ ጥላሁን ጀምበር ስም ይጻፍ እንጂ፤ የገዥውን ፍላጎት ለማሟላት የተዘጋጀ መልዕክት ነው። በቅማንቶች ላይ ለተደረገው በደል ይቅርታ መጠየቅ አለበት። ይህ ለኔ አጠያያቂ አይደለም። ይህ ደግሞ ለቅማንቶች የተወሰነ ሳይሆን፤ በሁሉም በደሉ በደረሰባቸው ኅብረተሰቦች ውስጥ አጠቃላይ መደረግ ያለበት ጉዳይ ነው። ነገር ግን፤ በደሉ አቶ ጥላሁንም እንዳሰመሩበት በሀገር መሪዎች የተደረገ በመሆኑ፤ አሁን ያለው ሀገረ-ገዥ፤ ባለፉት ገዥዎች ስም ይቅርታ እንዲጠይቅ መደረግ አለበት። የመንግሥት ለውጥ መካሄዱም የዚሁ ቀመር አንድ ገፅ ነው። በተጨማሪም አቶ ጥላሁን ጀምበር በመጀመሪያው ገፅ በሁለተኛው አንቀጽ መዝጊያ፤ *“አሁንም ቢሆን አልፎ አልፎ ጎሳን መሠረት ያደረጉ ግጭቶችና የንብረት ዘረፋ ወንጀሎች እንደሚከሰቱ ማሳያ ማስረጃዎች አሉ።”* በማለት አስፍረዋል። ይህን እኔ ስረዳው፤ ገዥው ክፍል ሀገር ማስተዳደር አልቻለም ወይንም ሆን ብሎ እያካሄደው ነው ማለት ነው! ታዲያ የማን ጥፋት ነው? ጉዳዩ ግን፤ የአምባገነኑ ወገንተኛ የትግሬዎች ነጫ አውጪ ግንባር ሾፌር ሆኖ፤ የተፈጥሮ ዕድገት ሂደትን በመጻረር፤ ይልቁንም የዕድገት ሂደቱን ቀኝ ኋላ ዞር ብሎ በመጋለብ፤ በገዥው ቡድን የፖለቲካ ፍልስፍና ስሌት በመታገዝ፤ ያካባቢ ዘውድ ለመጫን ሩጫ፤ አለያም በአቶ ጥላሁን ጀምበር ስም የገዥው የፖለቲካ ቅመራ ነው።

*ወደ መጀመሪያው ማጠያየቂያዬ ልግባ። የዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነው፤ “አሁን በኢትዮጵያ ያለው ሕገ-መንግሥት ትክክል ነው። የአማራ ክልል አስተዳዳሪዎች ሕገ-መንግሥቱን በትክክል ሳይተረጉሙ በደሉን!” የሚል አቤቱታ ነው። እግረ መንገዱን ደግሞ፤ “አማራ አና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን፤ የቅማንቱን ኅብረተሰብ አጥፍተዋል፣ በድለዋል፣ ቋንቋውን አምክነዋል፣ ከፍተኛ በደል ሠርተውብናል!” የሚል አቤቱታ አለው። በቀጥታ ቃል በቃል ከጦማራቸው ልጥቀስ፤ ሀ) “አብላጫ ያለው የአማራ ህዝብ በአንፃራዊነት አናሳ ቁጥር ያለውን የቅማንት ህዝብ ውጦ በኃይል የማንነት ለውጥ ለማምጣት ከጥንት አንስቶ እስካሁን ዘመን ድረስ በመሪዎች አስተባባሪነት ስራው እየተሰራ ነው።” ይሉንና ቀጥለው ለ) “ከዚህ ላይ ሊጠቀስ የሚገባው ትልቁ ችግር የቅማንት ህገ-ልቦና ሃይማኖት በውስጡ የያዘው ባህልና ትውፊት ስለሚታወቅ ይህን ሃይማኖት ለማጥፋት የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ቤተክርስትያን ከጥንት ጀምራ እስካሁን ድረስ የማትፈነቅለው ድንጋይ የለም።” ብለዋል። ይሄ ጽሑፍ፤ የናንተን እንጃ ለኔ ስብሃት ነጋን ስብሃት ነጋን ሸተተኝ! ባጭሩም አቶ ጥላሁን*

ጀምበር፤ *“እናንተ ፈራጆች ባትሆኑም፤ ቅማንት የሆናችሁ በቅማንትነታችሁ ተሰባሰቡ፣ ሌሎቻችሁ ደግሞ፤ በአማራ ክልል አስተዳደር ላይ ጫና አድርጋችሁ፤ አምባገነኑ ወገንተኛ የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት የፈቀደልንን መብታችንን እንድናስከብር እርዱን!”* ነው።

መቼም ፖለቲካ ማንኛውንም ጉዳይ በፈርጅ በፈርጅ አድርጎ ነው የሚያየው። አቶ ጥላሁን ጀምበር፤ ከርሳቸው ጋር አንድ የምስማማበትን ጉዳይ በመጀመሪያው አንቀጽ ላይ አስፍረዋል። *“ማንነት የራስ አስተዳደር መሠረት ነው።”* ብለዋል። አዎ! ኢትዮጵያዊነት የሀገራችን አስተዳደር መሠረቱ ነው። ትክክል ነዋት! በሀገራችን ኢትዮጵያዊ ያልሆነ ማስተዳደር የለበትም። መለኪያው ኢትዮጵያዊነት ነው። የትም ቦታ፤ እግራችንን ማሳረፍ በምንችልበት የኢትዮጵያ ክልል፤ ኢትዮጵያዊነት ነው፤ መሥራት ያለበት ሀገራዊ ሀቅ። ይሄን የርሳቸውን ጽሑፍ ስመረምረው፤ ከገዥው መንግሥት በላይ፤ የከፋፍሎ መግዛት የፖለቲካ ስሌትን ለማሳካት፤ አቶ ጥላሁን ጀምበር ተሯሯጭ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ። በዚህ ለኔ፤ ከገዢው የከፋ የሕዝብ ጠላት ሆነው አግኝቻቸዋለሁ። እንግዲህ በፖለቲካ አሰፋፈር መነጸር ሲታይ፤ ከገዥውም ሰፈር የበለጠ ተስፈንጥረውና ሶስተኛ ዘርፍ አብቅለው፤ ከሕዝቡ በተቃራኒ ቆመዋል ማለት ነው። የአማራ ክልል የተባለውን የኢትዮጵያ ክፍል የሚገዛው፤ በአማራው ስም፤ የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር ነው። እናም ሕዝብ ባንድ ወገን፣ የአምባገነኑ ወገንተኛ ገዢ ቡድን በሌላ ወገን፤ አቶ ጥላሁን ጀምበር ደግሞ ከገዢው ሰፈር ርቀው ሌላ ሰፈር አበጅተዋል። መብታቸው ነው። ለምን ግን ከኢትዮጵያ ውጪ ወደዚህ አምጥተው አሰራጩልን? መልሱ ለኔ ግልጽ ነው። በውጪ ሀገሮች ያለው ኢትዮጵያዊ፤ የመብትን ጉዳይ፤ የሀገር ዜግነት ጉዳይ አድርጎ፤ እኛ ኢትዮጵያዊያን ነን ያለ በመሆኑ፤ የለም ኢትዮጵያዊ ልትሆኑ የቻላችሁት፤ በኢትዮጵያዊነት የምትሉትን እርሱትና፤ ከአማራውም አልፋችሁ፤ ቅማንት ነን ብላችሁ ስትሰለፉ ነው! ማለታቸው ነው። ከንግዲህ ይሄን ኢትዮጵያዊ ነኝ የምትሉትን ሞኝነት አስወግዳችሁ፤ በየብቃያችሁ ተለጠፉ ነው! አሁን ግልጽ ሆነልን። አማራ ነኝ የሚለውንም ለማምከን በክልሉ ያለውን መከፋፈሉ ይረዳናል ማለታቸው ነው።

ሁለተኛው ደግሞ፤ ይሄን በሀገራችን ያለ ገዥ ባለሥልጣን፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሠረታዊ ብሎ የተቃወመባቸው የፖለቲካ ፍልስፍናና የአስተዳደር መመሪያው በጥያቄ ውስጥ እያሉ፤ የዚህ ጽሑፍ መልዕክት ምንድን ነው? የሚለው ነው። ከላይ በኢትዮጵያ ሕዝብና በገዢው አምባገነን ወገንተኛ የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት መካከል ያለው ልዩነት፤ ሕዝቡ *“እኛ በሀገራችን ኢትዮጵያዊያን ነን። በኢትዮጵያዊነታችን ደግሞ አንድ ነን፤ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያዊያን ናት!”* ማለቱ ሲሆን፤ አምባገነኑ ወገንተኛ ገዢ ቡድን ደግሞ፤ የለም ኢትዮጵያዊ የሚባል የለም። ሀገሪቱም የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች ናት የሚለው ፈሊጥ ነው። እና የዚህ ጽሑፍ አጠቃላይ መልዕክቱ ምንድን ነው። በውጪ የምትኖሩና ይሄንን የምታነቡ ሰዎች፤ ያለውን መንግሥትና ሕገ-መንግሥት ተቀበሉ። አማራና ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ጠላቶቻችን ናቸው። ሲያጠፉን ኖረዋል። በየትውልዳችን እንሰባሰብ። ያለው መንግሥት በያዘው ይቀጥል። አታስቸግሩ። ማለቱ አይደለም? ተሳስቶ ከሆነ ልታረም ዝግጁ ነኝ። መማርን የመሰለ ድንቅ ነገር የለም። ለኔ የሠጠኝ መልዕክት ይሄንን ነው። ታዲያ ይህ የአምባገነኑ ወገንተኛ ገዢ ቡድን መልዕክት አይደለም! የጸሐፊው ስም ጥላሁን መሆን ወይንም ጀምበር መሆን ምን ፋይዳ አለው!

eske.meche@yahoo.com    http://nigatu.wordpress.com